# ከጥናቱ ምን ተማርን
## የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የጥናት ሪፖርት
**2024-2025**

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ጸጋዎቻችን —ጊዜ፣ሰዎች እና ገንዘብ እንዴት ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሆነ ለመገምገም ከየትምህርት ሀብት ስልቶች(Education Resource Strategies )ጋር በመተባበር እየሰራ ነው፡፡ዓላማው የትኞቹ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየሰሩ እንደሆነ ማወቅ እና ተማሪዎች እና ሰራተኞች የተሻለ ተሞክሮ ወይም ውጤት እንዲያገኙ ለመርዳት ምን መሻሻል እንዳለበት መለየት ነው፡፡

## 1. ልምድ ያላቸውን መምህራን በእኩል አለማዳረስ

- በከፍተኛ የድህነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በብዛት ለሙያው አዲስ የሆኑ መምህራን አሏቸው (ከሶስት ዓመት ያነሰ የስራ ልምድ)፡፡ እነዚህ አስተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ብዙ ጊዜ ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- ጥቁር ተማሪዎች፣ባለብዙ ቋንቋ ተማሪዎች እና ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ለሙያው አዲስ የሆኑ ብዙ መምህራን በሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች የመማር እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡
- ከመምህራን ጋር የሚሰሩ አሰልጣኞች እነሱን ስኬታማ እንዲሆኑ ይረዷቸዋል፣ነገር ግን ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ መጠን እና የስነ-ሕዝብ አወቃቀር ካሏቸው ሌሎች ዲስትሪክቶች ያነሱ አሰልጣኞች ስላሏቸው እያንዳንዱ አሰልጣኝ ብዙ አስተማሪዎችን ይረዳል፡፡

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** ልምድ ያላቸው አስተማሪዎች እና ጠንካራ የድጋፍ ስርዓቶች ተማሪዎችን እንዲማሩ እና እንዲበለጽጉ ያግዛሉ፡፡

## 2. በከፍተኛ ትምህርት ምዝገባ ላይ ያሉ ክፍተቶች

- የአሜሪካን ህንዳውያን፣ሂስፓኒክ እና ጥቁር ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ እንደ Advanced Placement (AP) ወይም International Baccalaureate (IB) ባሉ ከፍተኛ ትምህርቶች የመመዝገብ ዕድላቸው አነስተኛ ነው፡፡
- ብዙ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲት እንዲያገኙ በሚያስችል ፕሮግራም በ Running Start በኩል የኮሌጅ ትምህርቶችን ይወስዳሉ፡፡ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የጥቁር እና የእስያ ተማሪዎች በ Running Start ይሳተፋሉ፡፡
- የሂስፓኒክ ተማሪዎች በክፍላቸው ጥሩ ውጤት ሲያስመዘግቡ እነዚያን ትምህርቶችን የመውሰድ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ምንም እንኳን ጥቁር ተማሪዎች ጠንካራ የትምህርት ውጤት ቢያሳዩም፣ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ አሁንም ክፍተቶች ወይም አለመመጣጠን ይታያል፡፡ይህ የሚያሳየው ትምህርቶቹ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች እንደማይሰጡ ወይም በትምህርት ቤቶቹ ፍትሃዊ ያልሆነ የጊዜ ሰሌዳ አወጣጥ መኖሩን ነው፡፡
- ወጥነት የሌላቸው የአካዳሚክ ድጋፍ ፕሮግራሞች እነዚህን ተግዳሮቶች ከባድ ያደርጉታል፡፡

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** የላቁ ኮርሶችን መውሰድ የሕይወት ዝግጁነት በሮችን ይከፍታል፡፡

## 3. የትምህርት ቤት መሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል

- በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን ለትምህርት ቤቶቻቸው ውሳኔ የማድረግ ብዙ ነፃነት አላቸው፣ነገር ግን 42% የሚሆኑት ከ0-2 ዓመት ልምድ ያላቸው ስለሆኑ እና ያንን ነፃነት በአግባቡ ለመጠቀም ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡
- በዚህ ዲስትሪክት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሱፐርቫይዘር ከሌሎች ተመሳሳይ ትላልቅ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ውስጥ ካሉ ሱፐርቫይዘሮች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡
- ከትምህርት ቤት መሪዎች መካከል ግማሽ የሚሆኑት ብቻ ከማዕከላዊ ቢሮ የሚያገኙት ድጋፍ የተደራጀ እና ለመጠቀም ቀላል እንደሆነ ይሰማቸዋል፡፡

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** ጠንካራ አመራር ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ጥብቅ እና ሁሉን አቀፍ የትምህርት ተሞክሮዎችን እንዲያቀርቡ ይረዳል፡፡

## 4. የገንዘብ ድጋፍ ሁልጊዜ ከፍላጎት ጋር አይጣጣምም

- ድህነት የትምህርት አፈፃፀምን በእጅጉ ይጎዳል፣ነገር ግን ተመሳሳይ የድህነት ደረጃ ያላቸው ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ውጤቶችን ያስመዘግባሉ።ማስተማርና አመራር ተጽዕኖ አለው።
- ከፍተኛ ቁጥር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተማሪዎች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ገንዘብ ሲያገኙ፣ አብዛኛው ገንዘብ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት እና የተለያዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ተማሪዎች ፕሮግራሞች ይውላል።
- አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት  ርእሰ መምህራን ብቻ ሀብቶች በፍትሃዊነት እንደሚከፋፈሉ ያምናሉ።

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልገውን ነገር እንዲያገኝ ሊረዳው ይችላል።

## 5. የፋይናንስ ድጋፍ ዘላቂነት አደጋ ላይ ነው

- በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የመምህራን ደመወዝ ወይም የሰራተኞች ወጪ ከፍተኛ ነው፣ ስለዚህ ዲስትሪክቱ እነዚህን ወጪዎች ለመሸፈን ከእኩዮቹ ዲስቲቶችቶች ጋር ሲነጻጸር ለእያንዳንዱ ተማሪ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ይፈልጋል።
- ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከሌሎች ትላልቅ ዲስትሪክቶች ይልቅ ብዙ ትናንሽ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ350 በታች ተማሪዎች ያሏቸው ሕንፃዎች) አሏቸው።
- ዲስትሪክቱ ለ2026-27 የ87 ሚሊዮን ዶላር የበጀት ጉድለት ይገጥመዋል፣ ይህም ከባድ ውሳኔዎችን ይጠይቃል።

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** የፋይናንስ ጤንነት ለእያንዳንዱ ተማሪ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት አስፈላጊ ነው።

## 6. የስትራቴጂ አፈፃፀሙ ግልጽ ያልሆነ እና የተበታተነ ነው

- ብዙ የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን እርዳታ ወይም መመሪያ ሲያስፈልጋቸው ማን ጋ መሄድ እንዳለባቸው ለማወቅ ይቸገራሉ።
- ከግማሽ ያነሱ ሰዎች የማዕከላዊ ቢሮ ቡድኖች ውጤታማ በሆነ መንገድ አብረው እንደሚሰሩ ያምናሉ።
- አስፈላጊ ፕሮጀክቶችን እና ስልጠናዎችን የሚመራው ማን እንደሆነ ግልፅ አይደለም።

**ለምን አስፈላጊ ሆነ:** Clear roles and coordination help schools implement strategies that improve student outcomes.

## ቀጣይ እርምጃዎች

ይህ የጥናት ትንተና ዲስትሪክቱ እያዘጋጀው ያለውን የስትራቴጂክ ዕቅድ ረቂቅ አቅጣጫ ይሰጠዋል። እንዲሁም የወደፊት በጀታችንን ለማቀድ ይረዳናል። ስለዚያ እቅድ በ የስትራቴጂካዊ እቅድ ሂደት ድረ-ገጻችን(Strategic Planning Process webpage) ላይ  የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።



**ሙሉውን የጥናቱ ሪፖርት ያንብቡ**

(እንግሊዝኛ ብቻ) ።